# የምፅዐቱ የምሥራች

ቅጽ 67 ቁጥር 5(797) «አምላካቸውን የሚያውቁ ሕዝቦች ይበረታሉ። (ዳንኤል 11÷32)

## ሁላችንም በመንታ መንገድ ላይ እንገኛለን።

«ኤልሳም፦ መንፈስህ በእኔ ላይ ሁለት እጥፍ ይሆን ዘንድ እለምንሀለሁ አለ። እርሱም አስቸጋሪ ነገር ለምነሃል፣ ነገር ግን ከአንተ ዘንድ በተወሰድሁ ጊዜ ብታየኝ ይሆንልሃል። አለዚያ ግን አይሆንልህም አለ» መጽሐፈ ነገስት ካልእ (2ኛ ነገስት) 2 ÷ 9-10።

### የእግዚአብሔር መገናፀፊያ

ኤልሳ የጠየቀው ጥያቄ እጅግ አስቸጋሪ፣ ከባድም ነው። በትክክል ኤልሳ የጠየቀው በሰው አስተሳሰብ ከባድ ቢሆንም በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ቀላል ነው።

በዚያ ዘመን የነበረው አስተዳደር እጅግ ብልሹ እርኩሰትና ጣዖት አምልኮን የሚያበረታታ ስለነበር የጌታን መጐናፀፊያ ክብርና ሀይሉን ማየት የነቢዩ ፍላጐትና መሻት ነበር። ዛሬም እግዚአብሔር አልተለወጠም። በሀገራችን ኢትዮጵያም ሆነ በዓለም ዙሪያ እርኩሰት፣ በደልና ኃጢአት እየሰፋ ፅድቅና ደግነት እየጠፋ ባለበት ዘመን ላይ ለመሆናችን የጌታ መንፈስ ያለበት ሁሉ ይገነዘበዋል።

የኤልያስ ታናሽ የነበረው ነቢይ ኤልሳ ከነቢዩ ኤልያስ የእግዚአብሔርን ኃይልና መጐናፀፊያ እንደተመኘው ሁሉ የዘመኑ የእግዚአብሔር ቤት አገልጋዮች ይህንኑ በእጥፍ ሊጠይቁ የተገባ ነው። ምክንያቱም ያለ ጌታ መንፈስ ቅዱስ አነሳሽነትና ድጋፍ የዘመኑን ተግዳሮት መቋቋምና የጠፉትን መመለስ አይቻልምና።

### ከጭንቀት የተነሳ የሚገኝ ፀሎት

ያለንበት ዘመን የእግዚአብሔር ቤት አገልጋዮች ከማንኛውም በላይ ቅዱስ መንፈሱን እጥፍ ሊጠይቁ የሚያስፈልግበት ዘመን ላይ እንገኛለን። ሁላችንም በመንታ መንገድ ላይ ነን። በጕውንና መልካሙን ነገር ግን ጠባብ የሆነውን የክርስቶስን መንገድ መያዝ ወይም ሠፊውንና ሁሉም የሚገባበትን የዓለምና የሠይጣን መንገድ መያዝ እና መከተል፤ ማንም ከእነዚህ ከሁለት መንገዶች ውጭ አይደለም። ሌላ አማራጭ ወይም አስታራቂ እና አግባቢ ወይንም ደግሞ አደራዳሪ መንገድ በክርስና የለም። በኢትዮጵያም ይሁን በአሜሪካ፤ በአውሮፓ ይሁን በአውስትራሊያ ወይም በእስያ ብንኖር ከሁለቱ መንታ መንገዶች በአንዱ እንጂ ከዚህ የተለየ ሌላ መንገድ አይኖረንም።

ከሁሉም የሚበጀን እና የሚሻለን፤ የተሻለውን መንገድ እና ሕይወት የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው (ዮሐንስ 14÷6)።

በሀገር ቤትም ሆነ በውጭ ሀገር ለእውነተኛ ዎቹ ክርስቲያኖች ዓለም አትመችም፤ መከራ አለባት። ስለዚህ የሚደርስብን ጭንቀት እንደ እስራኤል ልጆች ተገቢውን የጩኸት ፀሎት ወደ ጌታ እንድናቀርብ ያበቃናል።

«በተጨነቁ ጊዜ ወደ እግዚአብር ጮኹ፤ ከመከራም አዳናቸው»። (መዝሙር 106÷19)።

## ዘላቂው ጉዳይ እና የእኛ ምላሽ

የእግዚአብሄርን ቃል መሰበካችንና እንደ ኤልሳ በእግዚአብሄር መጉናፀፊያ የመንፈስ ቅዱስ ሀይል መሞላታችን ዘላቂ የሚሆነው እውነቱ ከአንደበት አልፎ በኑሮና በሕይወት በፍሬ ሲታይብን ነው።

የወንጌል ሰባኪ በእግዚአብሄር ሕግ መሠረት ሰው ሁኑ ቢፈተን ሁሉም በደለኛና ፍርድ የሚገባው መሆኑን ገልፆ ካስተማረ በኋላ በክርስቶስ ወንጌል ፀጋው በእምነት ከፍርድ እንደሚያድን ሊሰብክ ይጠበቅበታል። በዘላቂነትም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ እንደሚያነፃና ኃጢአታቸውን አምነው ለሚናዘዙ የኃጢአት ሐዋርያት የእግዚአብሔር ሙሉ ምህረት እንደተገባቸው ሊታወጅ ይገባል።

## የእግዚአብሔር መንፈስ ብቃትን ይሰጣል

በእግዚአብሔር ቤት አገልግሎት ወሳኙ ጉዳይ የሰዎች ጉልበት፣ ልምድና ጥበብ ሳይሆን የእግዚአብሔር መንፈስ ብቻ ነው። «ከመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር» (ትንቢተ ዘካርያስ 4÷6)

ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ ከባርነት ከግብፅ ምድር መርቶ ከማስወጣቱ በፊት የእግዚአብሄር መንፈስ በቁጥቋጦ እሳት ተገናኝቶት ነበር፤ ሐዋርያቱም ሺዎቹን ወደ ክርስቶስ መንግስት ለማስገባት የመንፈስ ቅዱስ እሳት አስቀድሞ ነክቷቸው ነበር።

ዛሬም ጌታ አልተለወጠም። የእግዚአብሔር አገልጋይ በሕይወቱ እንዲበረታና ብዙዎችን ከገሃነም ማትረፍ የሚቻለው መጀመሪያ መሪዎቹ በመንፈስ ቅዱስ እሣት ሲለኮሱ ነው።

## የክርስቶስ ወንጌል የሚሰበከው እና የእግዚአብሄር ክብር የሚገለፀው በመንፈሱ ነው።

«የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው። ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና» (ሉቃስ 4÷18) በክርስቶስ ዘንድ የነበረ ትሁት፣ ቅን፣ በጐ፣ የዋህ እና አዛኝ መንፈስ እስከሌለን ድረስ የእርሱን ወንጌል ለሌሎች ማካፈል አንችልም።

የቤተክርስቲያን ታሪክ እንደሚያረጋግጠው የእግዚአብሔር መንፈስ መጐናፀፊያ የወረደባቸው ብቻ በሀይልና በሥልጣን የጌታን አገልግሎት ለመፈፀምና ብዙዎችን ከስጋና ከመንፈስ ባርነት ነፃ ማውጣት ችለዋል።

እኒህ የእግዚአብሄር አገልጋዮች እውነተኛ ውን አምላካቸውን በሚገባ የሚያውቁና እርሱም የሚያውቃቸው ሲሆኑ ከጊዜ ወደጊዜም እየበረቱ በእርሱም ተስፋ በማድረግ እየታደሱ ከዘመን ወደ ዘመን ይሸጋገራሉ።

«እግዚአብሄርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ» (ኢሳይያስ 40÷31)።

## መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ

ከፊታችን ከተደቀነው መንታ መንገድ ላይ በአቸናፊነት ለመወጣት እራሳችንንም፣ ትውልዳችንንም ካለንበት የእርኩሰት ከበባ ለማትረፍና ከሚመጣው ቁጣ ለመዳን ዛሬም ብቃት የሚሰጠንን፣ የሚቀድሰንን፣ ቅዱሱን የእግዚአብሄር መንፈስ ልንቀበል ያስፈልገናል። እንዴት? እንደቃሉ።

«ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» (ሐዋርያት 1÷8)።

# የእግዚአብሔር ቤትን የሚመለከት ፀሎት

«የሠራዊት አምላክ ሆይ ማደሪያዎችህ እንደምን የተወደዱ ናቸው! ነፍሴ የእግዚአብሄርን አደባባዮች ትወዳለች፣ ትናፍቅማለች። ልቤም ሥጋዬም በሕያው አምላክ ደስ ተሰኙ፤ ወፍ ለእርስዋ ቤት አገኘች፣ ዋኖስም ጫጩቶችዋን የምታኖርበት ቤት አገኘች፣ የሠራዊት አምላክ ንጉሴም፤ አምላኬም ሆይ እርሱ መሠዊያህ ናቸው ለዓለምና ለዘለዓለም ያመሰግኑሃል» (መዝሙረ ዳዊት 83÷1-4).

በብሉይ ኪዳን ዘመን የእግዚአብሔር ሕዝብ አምላኩን በድንኳን በመቅደስና በተራራ ላይ ሲያመልክ የነበረ ሲሆን በአዲስ ኪዳን ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በግልፅ እንዳስተማረው ሥፍራ ሳይወስነው እግዚአብሔር ሕዝብ አምላኩን በእውነትና በመንፈስ ዘወትር በሁሉም ሥፍራ ያመልከዋል፣ ያከብረዋል (ዮሐንስ 4÷24)። የብሉይ ኪዳን አምልኮ ከአዲስ ኪዳን የሚለየው የእግዚአብሔር ሕዝብ እራሱ እግዚአብሔር ሕያው መቅደስ መሆኑ ነው። «እኛ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነንና» (1ኛ ቆሮንቶስ 3÷16፣ 2ኛ ቆሮንቶስ 6÷ 16)

ለእግዚአብሄር ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መስዋዕትን ታቀርቡ ዘንድ ቅዱሳን ካህናት እንድትሆኑ መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ (1 ጴጥሮስ 2÷5)።

በሁለቱም አቅጣጫ ክርስቲያኖች ሕዝባችን የግል ሕይወታችን ሆነ የምንሰበሰብበት ሕንፃና ቤት የእግዚአብሔር መቅደስ መሆኑን አስተውለን ልንጠነቀቅ ያሻል።

በዚህ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ የሚከናወኑ ድርጊቶች ሁሉ ጌታን የሚያስከብሩና ቃሉን የሚጠብቁ ሊሆን ያስፈልጋል። በእግዚአብሔር ስም ሰዎቹን የሚያዋርዱና የሚጨቁኑ፤ ዘርን ከዘር የሚያበላልጡና የሚያናክሱ መልዕክቶች እንዳይመጡ የሁሉም የእግዚአብሔር ቤት አገልጋይ ኃላፊነትና ግዴታ ይሆናል።

ለእግዚአብሔር ቤተመቅደስና ታቦት ግድ የሌለው ካህን ኤሊ ከነልጆቹ እንደተቀሰፈ ሁሉ ዛሬም ለእግዚአብሔር መቅደስና ቤተሰብ ግድ የማይሰጣቸው ሁሉ ከፍርድ አያመልጡም። እናስተውል፣ እንጠንቀቅ በእግዚአብሔር ቤት የመጀመሪያው ሥራ ፀሎት ነውና፤ በሰውነት መቅደሳችንም ሆነ በሕንፃ መሰብሰቢያችን ፀሎትን፣ የልብ ፀሎትን ቅድሚያ እናድርግ። «ቤቴ የፀሎት ቤት ትባላለች» (ማቴዎስ 21÷13)።

ኢየሩሳሌም ፅዮን ወይም ቅድስት ቤተክርስቲያን ተብላ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች የሚሰበሰቡባት ማህበር ከነገድ፣ ከወገን ከቋንቋ የተደባለቁ የተጠሩባት ህብረት ናትና እንከባከባት።

የቤተክርስቲያን መለያዋም የእግዚአብሔር ደህንነት የሚሰጥባቸው አገልግሎቶች ቅዱስ ጥምቀት፣ ስጋና ደሙ ናቸው።

## መልዕክት ከአማታሚው (ሬቨ ካርማይክል)

# የእግዚአብሔር ኃይል ለእናንተ ነው

«በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለጠግነት ምን እንደሆነ ለምናምንም ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንደሆነ ታውቁ ዘንድ ነው» (ወደ ኤፌሶን 1÷19)

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የምታምኑ አማኞች የሆናችሁ ለእናንተ የተዘጋጀ የእግዚአብሔር ኃይል አለ። እግዚአብሔር በሁሉም ሥፍራ ሊገኝ የሚችል

ሁሉን ቻይ ጌታ መሆኑንም ለአንድ አፍታ እንኳን እንዳትረሱ የእግዚአብሔር ሀይል አንዳች ገደብ የለውም ሐዋርያው ጴጥሮስ እንደፃፈልን «የእግዚአብሔር ጉልበት ሁሉን ያስችለናል። የመለኮቱ ኃይል በገዛ ክብሩና በበጐነቱ የጠራንን በማወቅ ለሕይወትና እግዚአብሔርን መምሰል የሚሆነውን ነገር ሁሉ ሰጠን» (2 ጴጥሮስ 1 ÷ 3)

## እግዚአብሔር ኃያል ነው

እግዚአብሔር በእራሱ ከተፈጥሮው መጀመሪያው ኃያል ነው። «እግዚአብሔር ብርቱና ኃያል ነው» (መዝሙር 23÷8)። እግዚአብሔር ቀኙ በኃይል የተሞላ ነው። አቤቱ ቀኝህ በኃይል ከበረ» (ዘፀአት 15÷6) እግዚአብሔር ብርታትንም የታጠቀ ነው። እግዚአብሄር ኃይልን ለበሰ፣ ታጠቀም ዓለምን እንዳትናወጥ አፀናት (መዝሙር 92 ÷ 1) ከእርሱ ከክርስቶስ ከእግዚአብሔር ልጅ የሚወጣ ቃል ድኩማንን ይፈውሳል፣ ያድናልም ከእርሱ ኃይል እንደወጣ አውቆ ከፀለየ በኋላ ኃይል ወደሌላ ሰው መሄዱን ተናግሯል።

## እግዚአብሄር ኃይሉን በክርስቶስ ሰጠን

ሰዎች ደካማ መሆናችንን ማንኛውንም በጐ ነገር በእራሳችን ፈቃድ ልንፈፅም እንደማንችል ፈጣሪ ተረድቶ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ጉልበትና ኃይሉን አፈሰሰልን፤ «መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ሀይልን ትቀበላላችሁ» (ሐዋርያት 1 ÷ 8) «ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሄር ሀይል ለማዳን ነውና» (ሮሜ 1÷ 16) «ሀይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ» (ፊልጵስዮስ 4÷13)

## በእግዚአብሄርና በሀይሉ ስመኑ

ዳዊት ታናሽ የመሰለው የእግዚአብሔር ሰው አስፈሪውን ግዙፍ ተዋጊ ጐልያድን ለመውጋት በሄደበት ጊዜ በእግዚአብሄር እንደታመነ ሁሉ በዚህ አስቸጋሪ አስፈሪ ዘመን በእግዚአብሄር ታምነን ለእርሱ ሥራ በእምነት እንውጣ። «በተገዳደርነው በእስራኤል ጭፍሮች አምላክ ስም በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ» (1 ሳሙኤል 17 ÷ 45)

ለእግዚአብሄር የሚሳነው የለምና የሚሰጠንም ስጦታ ከአእምሮ በላይ ነው። የፈዘዙ እስኪነቁ የጠፉ እስኪመለሱ፤ ያልዳኑ እስኪድኑ ድረስ ሥራውን እግዚአብሄር ይቀጥላል በፀሎት እንትጋ።

## መንፈስ ቅዱስ ስንደበትን ይገራል፤ ያሳምራል

አስተዋይ እናትና አባት ልጃቸው በሰላ ቢላዋ ሲጫወት ወይም ነበልባል እሳት ሲነካ ሲጣጣር ዝም አይሉትም። ስለቱ እንዳይቆርጠው ወይም ነበልባሉ እሣት እንዳያቃጥለውም ይከለክሉለታል።

እንደዚሁም ሁሉ ለበጐ ሥራና ምግባር መግባቢያ የምሥራቹንም ቅዱስ ወንጌል ማስተማሪያው አንደበት ተሳስቶ ፍጥረትን እንዳያበላሽ ጌታ መንፈስ ቅዱስ የአማኙን ልብ እየፈወሰ ከአፉ የሚወጣውን እየገራ ያሳምራል። «ንፁህ የሆነውን ነገር ሁሉ፤ ፍቅር ያለበትን ነገር ሁሉ መልካም ወሬ ያለበትን ነገር ሁሉ አስቡ» (ፊልጵስዮስ 4÷8)

በሀገራችን መልካሙ አባባል እንደሚያስተምረን «ከአነጋገር ይፈረዳል ከአያያዝ ይቀደዳልና» ዘወትር በምንናገረው የእግዚአብሄር ፅድቅና በጐነት እንጂ የስጋ ስራ ተገልጦ እራሳችንንም ሆነ ሌላውን የሚያፈርስ ንግግር እንዳይወጣን ንግግራችን የታረመና በእግዚአብሄር ቃል የተቃኘ ይሁን።

«ለማነፅ የሚጠቅም ማናቸውም ቃል እንጂ ክፉ ቃል ከአፋችሁ ከቶ አይውጣ» (ኤፌሶን 4÷29)

የእግዚአብሄር ሕዝብ በኃጢአት በወደቀበት ዘመን ቋንቋው (ንግግሩ በክፋት ተሞልቶ ለውድቀት በቅቷል)። በአዲስ ኪዳን በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ እግዚአብሄርና ሰው ሲታረቁ የሰዎች ንግግር የተገራና፤ በቋንቋ ቢለያዩም እንኳ የሚግባቡና የሚደማመጡ እንዲሆኑ መንፈስ ቅዱስ ታላቁን ሥራ ጀምሯል። «እያንዳንዱም በገዛ ቋንቋው ሲናገር ይሰማ ነበር። በልሳኖቻቸው ሲናገሩ እንሰማቸዋለን» (ሐዋርያት 2÷6/11)።

ሰዎች በሐሜትና በክፉ ንግግር ተሞልተው ደንዳና ልብ የሚኖራቸው ቀስ በቀስ ነውና የአንድን ሰው ክፋት ለመስማትም ሆነ ለሌላው ለመንገር አንፍጠን፣ይልቁንስ ክፉ ነገር እንዲወገድ በሰማነው ወቅት በፀሎት እንጋደል።

አንደበት እንደ እሣት ሆኖ ትልቁን እንደሚካና ደን የሚቀጠረውን ቤተሰብን፣ ሀገርንና ዓለምን ያቃጥላል፤ ያፈርሣልና በእግዚአብሄር ቃል በመመራት ንግግራችንን እንግራ!

«አንደበት እሳት ነው፤ የፍጥረትንም ሩጫ ያቃጥላል።» (ያዕቆብ 3÷6)

በንግግራችን ሰዎችን ማሣዘናችንን መንፈስ ቅዱስ በገለፀልን ጊዜ ንስኃ እንግባ፤ በንግግራችን የተጐዳውም ሰው ይቅርታ እንጠይቅና እንታረቀው ከሁሉም በላይ ሐሜታን ተቀብለን ለሌላው አናስተላልፍ የሚያማልንን ሰው በመገሠፅ እንዲፀልይ እንገረው፤ አንደበታችን ሁሉጊዜ ውበትና ለዛ ይኑረው። «ንግግራችሁ ሁልጊዜ በጨው እንደተቀመመ ይሁን» (ቆላስያስ 4÷6)

## የፀሎት ሰዎች የእግዚአብሔር ምርጦች ናቸው

ፀሎት የእግግዚአብሄርን ሥራ ለመስራት ትልቁና እጅግ አስፈላጊው መሣሪያ ነው። ሁሉም ነገር ባልተሳካበትና ተስፋ በተቆረጠበት ሰዓት የልብ ፀሎት ለጌታ ሲደረግ ውጤት ያመጣል፤ የእግዚአብሄር ኃይል ይገለፀል።

የእግዚአብሄርን ልዩ መሣሪያ የፀሎትን ምስጢር የተለማመዱ ሰዎች ድል አድራጊ የእግዚአብሄር ሠራዊት ናቸው። ዳንኤል፣ ሀና፣ ኤሊያስ፣ ኤልሳ፣ ጳውሎስና ሲላስ በመፅሐፍ ቅዱስ የሚጠቀሱ ሲሆን በቤተክርስቲያን ታሪክ ደግሞ ሰማዕታቱ ፖሊካርፕና ሲፓሬን የመከታካምቦ ሰማዕታትና መፅሐፍ ቅዱስን ከላቲን ቋንቋ ውጭ የተረጐመ ዊክሊፍ ጆን ሉተርና በኢትዮጵያም የተሀድሶ በኩር ደቀ እስጢፎ ይገኛሉ።

«እርሱ ይፀልያልና» ሐዋርያት 9÷11 የተባለለት ሐዋርያው ጳውሎስን ጌታ ደማስቆ መንገድ ከተገናኘው ቀን አንስቶ እስከ ሕይወቱ ፍፃሜ ለብርቱና ውጤታማ ፀሎት ብዙ የለፋና በፀሎትም ፍሬ ያፈራ ነበር።

ከጥንት ቤተክርስቲያን ዘመን ቀጥሎ በተከሰቱት ዘመናት የክርስቶስ የማዳን ፀጋ በሐሳዊ ጳጳሳትና የሐይማኖት መሪዎች እንደሸቀጥ ሲሸጥ በተሞከረው ዘመን ይህን ተቃውመው ወንጌሉን ወደ ትክክለኛ መንገድ የመለሱት የተሀድሶ ሰዎች የእግዚአብሄር ምርጦች የፀሎት ሰዎች ናቸው። በእነዚህ የተሀድሶ የፀሎት ሰዎች ትጋት ተዳፍኖ የነበረው ወንጌል ወደብርሃን ወጥቶ በአያሌ ሚሊዮናዊያን ትጋትና ሰማዕትነት እነሆ ዛሬ በዓለማችን በቢሊዮን የሚቆጠሩ የክርስቶስ አማኞች ሊገኙ በቅተዋል።

በፀሎት ምርጦች ትጋት በፈረንሣይ የደረሰው ዓይነት እልቂት፤ በጀርመን፣ በእንግሊዝና ስካንዴኔቪንያን እንዳይከሰት ትልቅ የምልጃ ሥራ ተካሂዷል።

በሀገራችን ኢትዮጵያም በግንቦት ወር 1983 ዓ.ም. በጊዜው በነበረው መንግስትና ተቃዋሚዎች ዋና ዋና ከተማዎችን ለመያዝ በነበረው ትንቅንቅ ደም እንዳይፈስ በጊዜው የተደረጉ ሐገር አቀፍ ፀሎቶች መስራታቸውን ዘጋቢው አይቷል፡፡

«ለምኑ ይሰጣችሁማል ፈልጉ ታገኙማላችሁ! መዝጊያን አንኳኩ ይከፈትላችኋል» (ማቲዎስ 7÷7)

## እድን ዘንድ ምን ላድርግ?

ክርስቶስ በመስቀል ላይ ስለፈፀመለት አሁን ማንኛውም ሰው ለመዳን አንዳች ነገር የሚሠራውና የሚከፍለው አይኖርም፡፡ የመዳን ቃልን ሰምቶ ማመንና በፀጋው የዘላለም ሕይወትን መቀበል ይጠበቅበታል፡፡ ይህን አልቀበልም የሚል ማንም ሰው ግን አይድንም፡፡

### ስለዚህም ሰው ይድን ዘንድ:-

1. በኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሄር ልጅ ማመንና ለቤተሰቡም እንዲሁ (ሐዋርያት 16÷3)
2. ከክፉ መንገድ መመለስና ኃጢአትንም በየጊዜው መናዘዝ (ሮሜ 3÷23 6÷23 ኢሳይያስ 55÷7)
3. በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የመዳን ፀጋን መቀበልና የክርስቶስን ስጋና ደም መውሰድ (ማቲዎስ 8÷19) (ሉቃስ 22÷19)፡፡

# ዓለም ዓቀፍ የፀሎት ርዕሶችና ዘገባዎች

## እርስ በእርሳችሁ ፀልዩ

«ስለ እናንተ እግዚአብሔርን ዘወትር እያሰብን በአባታችን በእግዚአብሔር ፊት ፀሎታችንን እናቀርባለን» (ተሰሎንቄ 1÷ 2)

የሚከተሉትን የልብ ፀሎት ደብዳቤዎች ከፊሊፒንስ ደሴቶች ከሚንማርና ከዩጋንዳ፣ ከቲቤትና ከፓኪስታን እናቀርብላችኋለን፡፡

## ከፊሊፒንስ ክርስቲያን እህት

ስለእናንተ እየፀለይን ያለነው በየጊዜው በምትልኩልን የምፅአቱ የምሥራች ጋዜጣ መባረካችንን ለመግለፅ ነው፡፡ ታጋሎግ በተባለው ቋንቋችን 81ኛውን ዕትም ለማንበብ በቅተናል፡፡ በሃገራችን ያለው የኑሮ ውድነት ክፉኛ ቢነካንም በጌታ ተደግፈን እርሱን እያከበርን የጌታን ዳግም ምፅአት በተስፋ በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን፡፡ ኢየሱስ አሁን እንዲመጣልንም እንመኛለን፡፡ አያሌ ህፃናት ተርበው ምግብ ፍለጋ ሲመጡ ማስተናገድ ባንችልም በፀሎት እየተጋደልን ጌታ ሲያደርግላቸው እያየን ነው፡፡ በትክክል ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለነፍስም፣ ለስጋም መፍትሄ ሠጭ ነው፡፡

## ከሚንማር

በጌታ ስም ሰላምታዬ ይድረሳችሁ! ድሮ በርማ በምትባለው ሀገራችን ሚንማር እጅግ የከፋ ድህነትን ብናይም ሰዎችን ከክፉ ልማድና ባርነት ነፃ የሚያወጣውን የጌታ ወንጌል በመስበክ ፍሬውንም በማየት ላይ ነን፡፡

## ከዩጋንዳ

ሁሉን ቻይ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሰላምታዬ ይድረሳችሁ በዩጋንዳ ምድር ጌታን በወንጌል መነቃቃት ጋዜጣ ማገልገል በመቻሌ ታላቅ ደስታ ይሰማኛል።

የሕያው ምንጭ ወንዝ የተሰኘውን የበረከት መፅሐፍ በቋንቋችን ተርጉሜ ሕዝባችን ከዚህ ከዘላለማዊ የሕይወት ምንጭ መንፈስ ቅዱስ እየጠጣ ይገኛል።

ባለፈው በሕመሜ ምክንያት ግንኙነቴ ቢቋረጥም በጌታ ተፈውሼ እነሆ አሁን አገልግሎቴን ቀጥያለሁ። ጌታ የተመሰገነ ይሁን! አሜን።

## ከቲቤት ኔፓል

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሰላም ይሁንላችሁ! በቲቤት የላሽ ቋንቋ የምፅአቱ የምሥራች ትርጉም እያዘጋጀን ለሕዝባችን በማቅረብ ላይ እንገኛለን። በኔፓል አንድ ሚሊዮን አማኞች ያሉ ሲሆን በዚህ የመነቃቃት ጋዜጣ የተነሣ መንፈሳዊ ተሀድሶ ቀጥሏል።

## ምሥጋና

በሚንማርና በዩጋንዳ ጌታ ስለሚሰራው ስራ በፊሊፒንስ ስላለው የጌታ ፈውስና አገልግሎት በቲቤት የወንጌል ሕትመት ለመሠራጨቱ ጌታ የተመሠገነ ይሁን።

## ምልጃ

ለየምፅአቱ አገልጋዮች ብርታትና ጥበብ የሀገር ቤቱን ስራ የሚያስተባብር ሰው ጌታ እንዲያዘጋጅ በፀሎት እንጠይቅ።

# የምፅአቱ የምሥራች የአማርኛው ትርጉም አዲስ ምዕራፍ

«ከፀሐይ መውጫ እስከ መግቢያው ድረስ የእግዚአብሄር ስም ይመስገን» (መዝሙር 12÷3)። እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በ1980ዎቹ መጀመሪያ ላይ በቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን የሰንበት ትምህርት አስተማሪ ጥያቄ መነሻነት እንግሊዝኛው ዕትም ትርጉም እንዲጀመር እግዚአብሔር በጐ ሀሳቡን በባሪያዎቹ ዘንድ አስቀመጠ። በዚያው ዘመን፣ በዚያው አካባቢ የአዲስ አበባ ወንጌላዊት መካነ ኢየሱስ የወጣቶች የውሎ ፕሮግራም ላይ የአማርኛው ትርጉም ንባብ ሲሰማ በተገለፀው ምላሽ የመጀመሪያውን ትርጉም እንዲያካሂድ ጌታ የተርጓሚውን ልብ አነሳሳ።

በእግዚአብሄር ፈቃድ የመጀመሪያው ትርጉም በንግድ ሥራ ኮሌጅ ህብረት አባል በቆንጅት ወልደማርያም ታይፕ ተደርጐ በ1983 ዓ.ም. ከእንግሊዝኛው ዕትም ጋር በመላው ኢትዮጵያ ተሠራጨ።

የትርጉሙ ሥራ ሂደትም በተገለጠው በአንባቢዎች ተሣትፎ እየተበረታታ በቋሚነት ሲቀጥል የትርጉሙን ሥራ ተርጓመውና አስተባባሪው ከመካነ ኢየሱስ የመፅሐፍት ሥርጭት አገልግሎት ጋር በበጐ ፈቃድ ፈፅሟል። አገልግሎቱ እስከ አሁን ድረስ ቀጥሎ በኢትዮጵያ፣ በሩቅ ምስራቅ፣ በአውሮፓ እና አሜሪካ ወደ 4500 ለሚደርሱ አንባቢዎች በማሠራጨት የጌታን ዳግም ምፅአት በማብሠርና አዳዲሶቹን ወደ ክርስቶስ መንግስት በመጥራት ላይ እንገኛለን። ለዚህ ሁሉ ክብር ምስጋና ለእግዚአብሔር ይሁን! አሜን።

ተርጓሚውና አስተባባሪው በ2002 ወደ አሜሪካ ከተጉዋዙበት ጀምሮ ባለቤታቸው ወ/ሮ

ፋንታዬ ግርማ የማስተባበሩን ኃላፊነት ወስደው እስከ ነሐሴ ወር 2007 ዓ.ም ድረስ ሲያገለግሉ ቆይተው እሣቸውም ወደ አሜሪካ አቅንተዋል::

ዛሬም ይህንኑ አገልግሎት ይህ ቤተሰብ በእግዚአብሄር ዘርነት ለመደገፍ ቃል እየገባ የሀገር ቤቱን የማስተባበር ሥራ ጌታ ሰው እንዲያዘጋጅ ፀሎታችሁ እንዲቀጥል እንጠይቃለን::

ይህንን አገልግሎት በመተባበር የሚያሳትምልን በአሜሪካን ሀገር በመጠነኛ ኑሮ የሚኖሩት አሳታሚው ሪክ ካርማይክልና የሥራ ባልደረቦቹን ጌታ ይባርካቸው::

ለአገልግሎቱ ብቸኛው ገቢ የአንባቢዎች መዋጮ ብቻ ነውና በዚህ መልካም ሥራ እንድትተጉ በፀሎትና በምክርም እንድትበረቱ አሳስባለሁ:: የክርስቶስ ባሪያ አደፍርስ ሀብቴ መካሻ::

## የምዕስቱ የምሥራች የወንጌል መነቃቃት
### የትርጉም አገልግሎት

**ትርጉም እና ቅንብር**

አደፍርስ ሀብቴ መካሻ
ሴንትሉዊስ - ሚዙሪ
አሜሪካ

**አሣታሚ**

ሪክ ካርማይክል
ሲሲሊ ሲንዲያና
አሜሪካ

**ስርጭት እና ገፀ-መሰክ**

ሲሰማቢጥ ባስሰዮስ
አዲስ አበባ፣
ኢትዮጵያ